

ፓኖራማ ቁጥር 74

የትዝብት አድማስ

ሐምሌ 19 ቀን 2009 ዓም

# <u>ሰንደቅ ዓላማችን</u>

የወያኔ ባለሥልጣኖች ሲያስነጥሳቸው መሀረብ ለማቅረብ የሚሽቀዳደሙት የመለስ ዜናዊ አሻንጉሊት ፓርላማ አባላት፥ ሰሞኑን በታዘዙት መሠረት የኢትዮጵያ ታሪካዊ ሰንደቅ ዓላማ እንደ አሮጌ ዕቃ ተቆጥሮ ወደ ቤተ - መዘክር ወርዳ እንዲዘጋባት መወሰናቸውን ይፋ አድርገዋል። ይህ ደግሞ ሲጠበቅ የነበረ በመሆኑ ማንንም አላስደነቀም ። ትላንት የሀገሪቱ ዕድሜ ከአንድ መቶ ዓመት አይበልጥም ያለና ሰንደቅ ዓላማዋንም የጫማ ማዘቢያ ብጣሽ ጨርቅ ብሎ ያወረደ ታሪክ የለሽ ዘረኛ ቡድን ፥ዛሬ ይህን አሳፋሪ የታሪክ ወንጀል መፈጸሙ አሁንም በድጋሚ የቱን ያህል ኢትዮጵያንና ዜጎቿን እንደሚጠላ በተጨማሪ የሚያረጋግጥ ነው ። ጥላቻ ደግሞ ራሱን ጠይውን እንጅ ተጠይውን አንዳችም ጉዳት እንደማያደርስበት በታሪክ ተደጋግሞ የተገለፀ ክስተት ነው ። በአረንጓዴ ፥ብጫና ቀይ ኅብረ-ቀለማት ያጌጠው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰንደቅ ዓላማ ፥በዘመናት ዕልፍ አዕላፍ መስዋዕት የተከፈለበት ፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለሕዘቦች መኩሪያ የሆነ ፤ የጥንታዊቷ ሀገራችን የነፃነት ምልክትና የአኩሪ ታሪካችን ልዩ መታወቂያ መሆኑ ከወያኔ ቡድኖች በቀር መላው ዜጋ ያምንበታል ። መላው የአፍሪካ ሀገራት በቅኝ ግዛት ስር በነበሩበት ዘመንም የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በነፃዋ ሀገር በኢትዮጵያ ሰማይ መውለበለቧን እየተመለከቱ እነርሱም አንድ ቀን ከቅኝ ግዛት ባርነት ነፃ ወጥተው የየራሳቸውን ሰንደቅ ዓላማዎች በነፃ ሀገሮቻቸው የሚያውለበልቡበትን ቀን በናፍቆት ይጠብቁ እንደነበር የነፃነት ተጋዳዮች በየንግግሮቻቸውና በየዓለም አቀፍ ስብሰባዎች ሲናገሩት የነበረ ነው ።ይህንን ለመዘከር ፥ የጋናውን መሪ ዶ/ር ክዋሚ ንኩርማህ

የኬንያውን መሪ ጆሞ ኬንያታን ፥ የታንዛኒያውን ዶ/ር ጁሊየስ ኔሬሬን ስሞች ብቻ ለአብነት ጠቅሰን እናልፋለን ።

ወያኔና በወያኔ ፓርላማ የተሰባሰቡት የታሪክ ኢምንቶች ይህን ያውቁታል ተብሎ ስለ ማይጠበቅ ፥የሀገራችን ታሪክ አንፀባራቂ ኮከብ በሆነው ሰንደቅ ዓላማ ቢያፍሩ አንደነቅም ። እኛ ግን ሰንደቅ ዓላማችን የሀገራችን ታሪክና ነፃነት መግለጫ ብሔራዊ ምልክታችን ስለሆነ እንኮራበታለን ።“እንኳን እኔ የኢትዮጵያን ስንደቅ ዓላማ ሲያይ ግመሌ ቀጥ ብሎ ይቆማል።” ብሎ የተናገረው ኢትዮጵያዊው የአፋር ተወላጅ በሀገሩ ስንደቅ ዓላማ የቱን ያህል እንደሚኮራና እንደሚመካ አረጋግጧል ። በማንነት ፍላጋ ዙሪያ ለሚንከራተት ፀረ ኢትዮጵያ ቡድን በሀገራችን አኩሪ ታሪክና ነፃነት ላይ ይህን ሁሉ ውርደት ሲፈፅም ፥ ይህ የዛሬው ኢትዮጵያዊ ትውልድ አንገቱን ደፍቶ ውርደቱን ይቀበላል ማለት ዘበት ነው ። ለዳግማዊ የካቲት ተዘጋጅቶ እንደሚጠብቅ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሚገባ ያውቀዋል ። ጠቅላላ የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ ሁኔታ ለመለወጥ፥ሀገር አቀፍ ሕዝባዊ አመፅ የሚያስፈልግ ለመሆኑ አንድና ሁለት አይባልም ። ያን ጊዜ ዛሬ የተዋረደችው የሀገራችን ሰንደቅ ዓላማ በኢትዮጵያ ተራሮች በመሉ ከፍ ብላ ትውለበለባለች።

“ ትግላችሁን ቀጥሉ ከናንተው ጋራ ነኝ
ከሙዚየም ዋሻ ማን ቀብሮ ሊያስቀረኝ ። ”

እያለችን ነው ዛሬ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ !

ማነኛውም ነፃ ሀገር የራሱን ታሪክ፥ነፃነት፥ ማንነትና ኀልውና የሚገልፅበት ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማውን በኩራትና በይፋ የሚያውለበልበው፥ ከሌሎቹ የዓለም ሀገሮች ጋር በዕኩልነትና ከበሬታ በተጎናፀፈ ደረጃ ሊኖር እንዲያስችለው ነው። የዲፕሎማቲክ ፥የንግድ፥የስፖርት፥ የሰላም፥ የልማትና የትምህርት፥የባኅል፥ የሳይንስና የምርምር ግንኙነትና ትብብር ለማድረግ የሚጠብቀውን ተቀባይነትና ዕውቅና ማግኘት የሚችለውም የራሱን ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ አክብሮ ሲገኝ ነው። መላው የሀገሪቱ ህፃናት የሀገራቸውን ብሔራዊ መዝሙር ለማክበር በሀገራቸው ስንደቅ ዓላማ ዙሪያ ቢዘምሩ ከወያኔ በቀር ማንም ዜጋ አይከፋውም። ለመላው የአፍሪካ ሀገሮች የነፃነት ትግል ተምሳሌት የነበረችው የሀገራችን ሰንደቅ ዓላማ ፥ ዛሬ በነመለስ ዜናዊ የጥንት ታሪክ እንደሌላት ተቆጥሮ ፥ ቤተ መዘክር ውስጥ እንደ አሮጊ ጨርቅ እንድትወረወር መደረጉ ፥ ለኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ትልቅ የምስራች ሲሆን፥ ለዜጎቿና ለወዳጆቿ ግን መሪር ሀዘንና ፀፀት ነው ። የዜጎቿና የወዳጆቿ ሀዘንና ፀፀት ግን ለዘለዓለም አይሆንም ። ይህንን በዕርግጠኝነት ማናገር እንችላለን ። ለአምስት ዓመት

በፋሽስቶች እስካርባ ( ጫማ) ተረግጣ የተዋረደቸው ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማችን እንኳ ÷ በጀግኖቿ አባቶቻችንና እናቶቻችን የአርበኝነት ትግልና መሥዋዕት ከወደቀችበት ተነስታለች፡፡ይች ዛሬ የሀገራቸውን ታሪክ በማያውቁ አሳፋሪና ከሀዲ ቡድኖች የተዋረደችው ሰንደቅ ዓላማ÷በኢትዮጵያ የግዛት ክልል ብቻ ሳትወሰን ÷ ክብሯና ሞገሷ በዓለም አቀፍ ደረጃም የተከበረና የተደነቀ ነበር ፡፡ ዘርዓይ ደረስ በሮማ ከተማ ጣሊያኖች ያዋረዷትን ስንደቅ ዓላማ አላይም በማለት ጀብድ ሰርቶ የተሰዋው በከንቱ አልነበረም ፡፡ ሰማዕቱ አብዲሳ አጋም ÷ ከይጎዝላቪያ የነፃነት አርበኞች ጋር ተስልፎ ጣሊያኖችን የተዋጋው÷ የሀገሩን ሰንደቅ ዓላማ አንግቦ ነበር ፡፡ የአካል ጥንካሬውን መላው የዓለም ሕዝብ ያደነቀውን የማራቶኑን ጀግና በሮምና በሜክሲኮ ከተሞች 26 ኪሎ ሜትር ሮጦ ከአቸነፈ በኋላ የስፖርት አደባባዮቹን (ስታዴዮሞቹን) ሦስት ጊዜ የዞረው አበበ በቂላ ÷ የሀገሩን ሰንደቅ ዓላማ ከፍ አድርጎ በማወለብለብ ነበር ፡፡ ማሞ ወልዴም ለሰንደቅ ዓላማው ያለውን ክብር በተመሳሳይ ፍቅርና ጀብድ ገልጾታል ፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ÷ ለዘመናት የሀገሩን ነፃነት ÷የግዛት አንድነትና የብሔራዊ ልዕልና ሲያከብር የኖረው÷

“ **አክብር ሰንደቅ ዓላማህን ÷ ውደድ ሀገርህን !** ” የሚለውን የአንድነት መዝሙር እየዘመረ በያቅጣጨው የመጣውን ጠላት ድባቅ ሲመታ ኖሯል ፡፡ እንደማነኛው ነፃ የዓለም ሀገሮች ሕዝቦች ÷የኢትዮጵያ ሕዝብም በበኩሉ ÷ የሀገሩን ሰንደቅ ዓላማ ÷ ከታሪኩ ከነፃነቱ ÷ ከባኅሉ ÷ከማንነቱና ከሰብዕናው ለይቶ አያየውም ፡፡ በመሆኑም በሰንደቅ ዓላማው ይኮራል እንጅ አያፍርበትም ፡፡ለሰንደቅ ዓላማው ክብርና ሞገስ ይዋደቅላታል እንጅ ÷ በችንፈት አንገቱን በመድፋት ውርደቱን አይቀበልም ፡፡ ዛሬ ወያኔ በሀፍረት ወደ መታሽጊያ ቤት ገብታ እንድትጻፈን ያደረጋትን በአረንጓዴ ÷ ብጫና ቀይ ኅብረ ቀላማት ያጌጠችውን ብሔራዊ ስንደቅ ዓላማ ÷ በድልና በኩራት በኢትዮጵያ አደባባዮችና ተራሮች ላይ ያውለበልባታል ፡፡

ምናልባት ዛሬ ይህን ሁኔታ የተመለከተ የውጭ ተመልካች÷ “ ሞኝ ልጅ÷ ለአባቱ ተስካር ማውጫ በታረደ በሬ ፊኛ ይጫወታል፡፡ ” ብሎ ሊተርትብን ይችል ይሆናል፡፡ ከተረተብንም አንቀየመውም ፡፡ ምክንያቱም ÷ ተረቱ የተተረተብን÷ ከቁጭትና ለኢትዮጵያ ከመቆርቆር ነው ብለን ለማመን ስለምንፈልግ ነው፡፡ እንዲያውም በአሁን ወቅት÷ ኢትዮጵያ ሀገራችን የሚያዝንላትና የሚደግፉት የቅርብ ጎረቤትም ይሁን የሩቅ ዘመድ የሌላት መሆኑን ስለምንገነዘብ ÷ ለሀገራችን የሚቆረቆሩትን ስናገኝ በፀጋ እንቀበላቸዋለን ፡፡ በሀገር በቀል ከሃዲዎች በየጊዜው በመጥፋት ላይ ያለች ሀገር ጨርሳ ከመጥፋት ለመዳን ከፈለገች÷ በተቻለ መጠን አጥፊዎቿን ለማጥፋት በምታደርገው ትግል ከየትኛውም አቅጣጫ አስፈላጊውን ርዳታና ትብብር ማግኝት ይኖርባታል ፡፡ በተለይም የጥቁር ሕዝቦች የነፃነት

አርዓያና ተምሰሌት መሆኗን የሚገነዘቡላት የአፍሪካ አህጉር ሕዝቦች ፥ ኢትዮጵያ የትላትናዋ ባለውለታችን ነበረች ብለው ዛሬ በችግሯ ወቅት የሚተባበሯት ከሆነ ፥ በዕርግጥ እሰየው የሚባል ይሆናል ። ከቅኝ ግዛት ነፃ ከወጡት በርካታ የአፍሪካ ሀገራት መካከል ነፃነታቸውን ሲያገኙ ከያዙት ሰንደቅ ዓላማ ከአንዱ ወይም ከሌላው ኅብረ-ቀለም ወስጥ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ቀለም መጨመራቸው የታወቀ ነው ።ታዲያ አሁን ለአለው የኢትዮጵያ ትውልድ ለሰሚው ግራ ሊሆንበት የሚችለው ፥ በዘመናት፥ ታላቅ ታሪክና ዝና የነበራት ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማው፥በመላው ዓለም ሳይቀር በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች የራሷ ልጆች ያስተዋወቋት ስንደቅ ዓላማው፣ በዛሬ ገዥዎቿ በአደባባይ መውለበልቧ ቀርቶ፥ወደ መዘክር ዋሻ እንድትገባ የተፈረደባት መሆኗ ነው ። የሀገር ሰንደቅ ዓላማ ክብርና ታሪክ ጉዳይ በወቅቱ በዚያ ሀገር ላይ ሥልጣን በያዘና በተቃዋሚ ክፍሎች መካከል የሚደረግ ክርክርና ጠብ ብቻ ተወስኖ ሊታይና ሊቆጠር የሚገባው ነገር አይደልም ። ወይም በወያኔና በኢሕአፓ መካከል እንዳለው የማይታረቅ ቅራኔ ሆኖ የሚፈረጅ አይደለም ። ኢሕአፓ ከወያኔ ጋር ያለው የሞትና የሽረት ትግል በሀገራችን በኢትዮጵያ ባለው ብሔራዊ የዘለቄታ ጥቅምና ክብር እንዲሁም ህልውና ላይ ነው ። የኢትዮጵያ ብሔራዊና ታሪካዊ ስንደቅ ዓላማ ጉዳይም ከዚህ ዐብይ የሀገር ጉዳይ በተለየ መልኩ ሊታይ አይገባውም ። ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ የቅድሚያ አጀንዳ ፥ ኢትዮጵያን ከዘረኞች ጥፋት ማዳን መሆኑን ማነኛውም ዜጋ ያምንበታል ። ኢትዮጵያ ከዳነች ደግሞ ፥ የተዋረደቸውና እንደ አሮጌ ጨርቅ እንደትወረወር የተፈረደባት ሰንደቅ ዓላማችን ከተዋረደችበት ወጥታ እንደ ጥንቱ እንደ ጧቱ በአደባባይና በኢትየጵያ አድማስ ትውለበለባለች ። ይህ ደግሞ ምኞት ሳይሆን ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ የትግል ቃለ-ኪዳን ነው።